# የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግልን ኣላማ ለማስቀልበስ በወያኔ የሚፈጸም ወደር የለሽ ወንጀል

የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል መሰረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ኣተኩሮ የሚካሄድ ነው። የትግሉ ዋነኛ ኣላማ የኦሮሞ ህዝብ በሃገሩ ላይ የሃገር ባለቤትነት መብቱን እንዲጎናጸፍ ማስቻል ነው። ስለሆነም ትግሉ ይህንን ዋነኛ ኣላማውን ከግቡ ለማድረስ በጨቋኞኙ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ብሄር ወይም ህዝብ ላይ ኣያነጣጥርም። ትግሉ ከኣንድ ብሄር በመውጣት የጭቆና ኣገዛዝን በዘረጋ ገዢ ቡድን ላይ እንጂ ገዢ ቡድኑ የወጣበትን ብሄር በደፈናው በጠላትነት ኣይፈርጅም። የኦሮሞ ህዝብ የተነጠቀውን የተፈጥሮ መብቱን መልሶ በመጎናጸፍ ከኣጎራባቹ ህዝቦች ጋር በሰላምና በመከባበር መኖርን ይሻል።

የወያኔ ቡድን የኢትዮጵያ መንግስት ስልጣን ከጨበጠበት ወቅት ኣንስቶ የኦሮሞን ህዝብ የነጻነት ትግል ኣቅጣጫ ለማሳት ከመጣርና በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል የጠላትነት መርዝ ከመርጨት የተቆጠበበት ወቅት የለም። የኦሮሞ ህዝብ ትግል በሌሎች ዘንድ እንዲወገዝና በጥርጣሬ ኣይን እንዲታይ ለማድረግ የተለያዩ ሴራዎችን ሲሸርብ ቆይቷል። የኦነግን ፍትሃዊ ኣላማ ኣይኑን ጨፍኖ በመካድ “ኣሸባሪ” ብሎት በምክር ቤቱ ኣውጇል። ኦሮሞን ከተለያዩ የጎርቤቱ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ጋር በማጋጨት ደም ኣቃብቷል። ከፍተኛ ዋጋ ያለው ንብረትም እንዲወድም ምክንያት ሆኗል። ተመሳሳይ ጥፋቶችን ለመፈጸም ስርኣቱ የሚሸርባቸው ሴራዎች ተዘርዝረው የሚያልቁ ኣይደሉም።

የዚህ ጽሁፍ ኣላማ የወያኔ መንግስት የፈጸማቸውን ደባዎች ሁሉ ለመዘርዘር ኣይደለም። ከደባዎቹ መካከል ግን ቢያንስ በትምህርት ተቋዋማት ኣካባቢ በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ስርኣቱ የፈጸማቸውንና እየፈጸማቸው የሚገኘውን ከነማስረጃዎቹ በጥቂቱ ለመግለጽ ያህል ነው።

ኣስተዳድራቸዋለሁ የሚላቸውን ህዝቦች የሚፈራ መንግስት እነዚያን ህዝቦች ሁል ጊዜም በጥላቻ ኣይን ይመለከታል። ሁሌም ሰበብ ኣስባብ እየፈጠረ የዚያን ህዝብ ወይም ብሄር ኣባላትን ማሰር፣ መግደልና ኣፍኖ መሰወር ላይ ያተኩራል። የወያኔም ተግባር ከዚህ የተለየ ኣይደለም። እንዲህ ያለው ሰቆቃ እየተካሄደባቸው ከሚገኘው የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ኣንዱና ዋነኛው የኦሮሞ ህዝብ ነው። ከኦሮሞ ህብረተሰብ መካከል ደግሞ ጥቃቱ ይበልጥ ኣነጣጥሮ የሚታየው በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ነው ማለት ይቻላል።

በወያኔ መንግስት ባለልጣናት ተወጥኖና በስርኣቱ የደህንነት ሃይሎች ተቀናጅቶ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ የትምህርት ተቋዋማት ኣካባቢ በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ያነጣጠረ የትንኮሳ ደባ ላለፉት 10 ኣመታት ሳያቋዋርጥ እየተፈጸመ ይገኛል። ወያኔ የኦሮሞ ተማሪዎችን ማዋከብ፣ ማሰር፣ ማቁሰል፣ ኣፍኖ መሰወርና ከትምህርት ገበታ ማባረርን ኣንዲሁም ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ማጋጨትን መለያ ተግባሩ በማድረግ የጥላቻና የፍርሃት ስሜት በተማሪዎቹ መካከል ኣንዲስፋፋ ሲሰራ ከዛሬ ደርሷል።

ጥር 5 ቀን 2013 በፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ ኣራት ኪሎ ጊቢ የተቀሰቀሰውና የኦሮሞ ተማሪዎች ተለይተው በገፍ እንዲደበደቡ፣ ኣንዲቆስሉና በመቶዎች ለእስራት እንዲዳረጉ ምክንያት የሆነው ኣመጽም በወያኔ መንግስት ተወጥኖ ተግባራዊ የሆነውና ኣንድም ጊዜ ሳይቋዋረጥ ተግባራዊ በመሆን ላይ የሚገኘው የግጭት ሴራ ኣካል ነው። ጥር 5 ቀን 2013 የተፈጸመው ድርጊት የወያኔ ሴራ ውጤት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ባለፉት 12 ኣመታት በተለያዩ የሃገሪቷ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የተከሰቱትን ተመሳሳይ ክስተቶች መለስ ብሎ ማስታወሱ በቂ ይሆናል።

ባለፉት ኣመታት ውስጥ በየዩኒቨርሲቲዎቹ ሁሉ ሲከሰት የኖረው የግጭት መንስኤ ሁሉ ተመሳሳይ ነው። የገጭቶቹ መንስኤዎቹ ሁሉ የኦሮሞን ህዝብ ብሄራዊ ስነ ልቦና ይጎዳሉ

በተባሉት የጸብ ኣጫሪነት ስልቶች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። ሆን ብሎ የኦሮሞን ህዝብ ታሪክ ኣዛብቶና እያንቋሸሹ ማስተማር ኣንዱ መንስኤ ነው። ኦሮሞ ራሱን የሚጠራበትን ብሄራዊ ስሙን ሆን ብሎ ባለመጠቀም የጥላቻ፤ የንቀትና የዘለፋ ስም እየተጠቀሙ ኦሮሞን ያስቆጣሉ። የኦሮሞን ህዝብ ስምና ክብር የሚያዋርድና የሚዘልፍ መልእክት የያዙ ካናቴራዎችን እየለበሱ የጥላቻ ዘመቻ ያካሄዳሉ። የኦሮሞ ተማሪዎች ለይስሙላም ቢሆን ኣለ በሚባለው ህገ መንግስት ላይ ተመርኩዘው መብታቸው እንዲከበርና የትንኮሳ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ወገኖች ለህግ ኣንዲቀርቡ ሲጠይቁ መሳለቂያ ይደረጋሉ። ከዚህ ኣልፎ ይደበደባሉ፤ ይታሰራሉ፤ ለኣካል ጉድለት ይዳረጋሉ፤ ከትምህርት ገበታ ይባረራሉ። ከዚህ ሁሉም በላይ ይገደላሉ። እነዚህ እንግዲህ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ኣየተፈጸሙ የሚገኙ ታሪክ ይቅር የማይላቸው ወንጀሎች ናቸው። ለማስረጃ ያህል ከ2000 ኣ.ም. ጀምሮ በፍንፍኔ፤ በሃረማያ፤ በባህር ዳር፤ በኣዳማና በኣርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲዎች በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ያነጣጠሩትን ስነልቦናዊና ብሄራዊ ጥቃቶችን እንመልከት።

*ታህሳስ 21 ቀን 2000 በፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ*

በትውልድ ከትግራይ የሆነና ጌታቸው የተባለ የዩኒቨርሲቲው መምህር በትምህርት ክፍል ውስጥ በጥናታዊ ጽሁፍ ተብዬ ስራው የኦሮሞን ህዝብ ታሪክ ሆን ብሎ ኣንቋሸሸ። በዚህ ወቅት የክፍሉ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች የግለሰቡን የጥቃት ኣላማ በመቃወማቸው ወዲያው የጊቢው የጥበቃ ሃይል ተጠርቶ ኣስር የሚሆኑትን የኦሮሞ ተማሪዎች ይዞ ሄደ።

የተያዙት ተማሪዎች ድብዛቸው በመጥፋቱ ስጋት ውስጥ የወደቁ የዩኒቨርሲቲው የኦሮሞ ተማሪዎች ተሰባስበው ወልዴ ገሪማ ለተባለው የዩኒቨርሲቲው ኣስተዳዳሪ ኣመለከቱ። ኣስተዳዳሪ ተብዬው ኣውቆ እንዳላወቀ በመሆን ለጉዳዩ እንግዳ መሆኑን ነገራቸው። ከዩኒቨርሲቲው ኣስተዳደር ተገቢውን ምላሽ ያላገኙት ተማሪዎቹ ከሁሉም ጊቢዎች ከተውጣጣቱት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ጋር በመሆን በትምህርት ተቋዋሙ ውስጥ ሰፍሮ ለሚገኘው የፖሊስ ሃይል በማመልከት ታፍነው ደብዛቸው ስለጠፋ ወገኖቻቸው መረጃ ጠየቁ። ተማሪዎቹ በዚህ መልኩ ላቀረቡት ፍትሃዊና ሰላማዊ ጥያቄ የተሰጣቸው ምላሽ ልዩ የፖሊስ ሃይል ከውጭ በማስጠራት ተማሪዎቹን ማስደብደብ ሆነ። በዚህ እለት በዚሁ ምክንያት ተደብድበው ለኣካል ጉድለት የተዳረጉትን ተማሪዎች ስም መዘርዘር ይቻላል። በእለቱ ከታሰሩት ከመቶ የሚልቁ ተማሪዎች መካከል 18ቱ ተማሪዎችን ለኣመጽ ቀሰቀሳችሁ ተብለው ወደ ማእከላዊ ኣስር ቤት ተወስደው ለባሰ ሰቆቃ መዳረጋቸውን ታሪክ ያስታውሳል።

*የካቲት 2006 በባህር ዳርና በጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች*

የወያኔ መንግስት ለቅጥረኞቹ የተለያዩ ስልጠናዎችን ኣየሰጠ በባህር ዳርና ጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ሰርጎ በማስገባት የኦሮሞ ተማሪዎችን እንዲዘልፉና ትንኮሳ እንዲፈጽሙ ኣደረገ። በሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ትንኮሳ ፈጻሚዎቹ ለህግ እንዲቀርቡ ጠየቁ። የኦሮሞ ህዝብ ብሄራዊ ስምና ማንነቱ ይከበር ብለው ኣመለከቱ። በዚህ ወቅት በተለያዩ ብሄር ተወላጅ በሆኑት ተማሪዎች መካከል ጥላቻና መጠራጠር እንዲሰፍን ስለተፈለገ የኣማራ ብሄር ተወላጅ በሆኑ ተማሪዎች በኩል በኦሮሞ ላይ ያነጣጠሩ ዘለፋዎች እንዲሰሙ ተደረገ። ዩኒቨርሲቲዎቹ በሚገኙባቸው ከተሞች ውስጥ በኣፋን ኦሮሞ መነጋገር ክልክል መሆኑ ለኦሮሞ ተማሪዎች ተነገረ። በመሆኑም በከተሞቹ ውስጥ እርስ በርሳቸው ኣልያም በሞባይል ቴሌፎን ኣፋን ኦሮሞ ሲናገሩ የተገኙ ተማሪዎች ተደበደቡ። ኣሳዛኙ ነገር በቁጥር ትንሽ የማይባሉ የኣማራ ተወላጅ ተማሪዎችም የወያኔ መንግስት የጥፋት ሴራ መሳሪያ ሆነው ማገልገላቸው ነው።

*ነሃሴ 2006 በሃረማያ ዩኒቨርሲቲ*

የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች የኦሮሞን ስምና ማንነት የሚያንቋሽሽ ጽሁፍ የያዘ ካናቴራ ለብሰው በጊቢው ውስጥ ሲዘዋወሩ ተገኙ። ይህን ትንኮሳ የተመለከቱ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች የህዝባቸው ስምና ማንነት እንዲከበርና በዚህ አፍራሽ ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ተይዘው ለህግ አንዲቀርቡ በሰላማዊ መንገድ ጠየቁ። የተሰጣቸው ምላሽ ግን አግኣዚ የተባለውን የወያኔ ልዩ ሃይል ወደ ዩኒቨርሲቲው አስገብቶ በማስፈር የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ የጭካኔ ክንዱን እንዲሰነዝር ማድረግ ነበር። የኦሮሞ ተማሪዎች ለብሄራቸው ስምና ክብር በመቆርቆራቸው ብቻ ከመደብደብ በተጨማሪም ከትምህርት ገበታ ተባረሩ። በሃረማያ የተከሰተው ይህ ችግር ወደ ኣዳማና ጅማ ዩኒቨርሲቲዎችም በመዛመቱ በርካታ ቁጥር ያላቸው የኦሮሞ ተማሪዎች ከትምህርት ተባረሩ። ከሃረማያ ዩኒቨርሲቲ 42፣ ከኣዳማ ዩኒቨርሲቲ 20 እንዲሁም ከጅማ ዩኒቨርሲቲ 23 ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ተባረሩ። ከትምህርት የተባረሩትን የነዚህን ተማሪዎች ስም ዝርዝር ማቅረብ ይቻላል።

*መጋቢት 2009 በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ*

ለሁለተኛ ጊዜ በዚህ ዩኒቨርሲቲ በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ተከሰተ። ወያኔ በተማሪነት ሽፋን ወደ ጊቢው ያስገባው መንግስታዊ ቅጥረኛ ለኦሮሞ ህዝብ ያለውን በጥላቻና በንቀት የተሞላ ስሜት በአደባባይ ሲገልጽ ተስተዋለ። የኦሮሞ ተማሪዎች በደም ፍላት ወደ ሁከት ከማምራት ተቆጥበው ሁሉም ህዝቦች እኩል ናቸው በተባለበት ህገ መንግስት በምትተዳደር ሃገር እንዴት የኦሮሞ ህዝብ ክብር ይዋረዳል ብለው በሰላማዊ መንገድ ጠየቁ። የተሰጣቸው ምላሽ ድብደባና ወከባ ነበር። በዚሁ ወቅት 80 የሚሆኑት ተማሪዎች ታሰሩ። ኣጋዚ በተባለው ርህራሄ ቢስ የስርኣቱ ልዩ ቅልብ ጦርም ክፉኛ ተደብድበው ኣንዳንዶቹ ለኣካል ጉድለት ተዳረጉ።

*ግንቦት 2010 በፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ*

በትግራይ ተወላጅ ተማሪነት የተመሰሉ የስርኣቱ የደህንነት ኣባላት በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች መካከል ተሰግስገው ኦሮሞን ከሁሉም የሃገሪቷ ብሄሮች ለይተው በማንቋሸሽ የጥላቻና የንቀት ስሜት ያዘለ መልእክታቸውን ኣስተላለፉ። የኦሮሞ ተማሪዎች አሁንም ይህ ወንጀል በመሆኑ ህጋዊ ምላሽ ማግኘት እንዳለበት ለዩኒቨርሲቲው ኣስተዳደር በሰላማዊ መልኩ ኣመለከቱ። የተሰጣቸው ምላሽ የኣጋዚን ቅልብ ጦር ጠርቶ የኦሮሞ ተማሪዎችን ለይቶ በመደብደብ ኣካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት እንዲያደርስባቸው ማድረግ ሆነ። በዚህ ወቅት በደረሰው የጭካኔ እርምጃ የታሰሩትንና ኣካላዊ ጉዳት የደረሰባቸውን የኦሮሞ ተማሪዎች ስም ዝርዝር ማቅረብ ይቻላል።

*ሚያዝያ 2011 በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ*

ከዚህ በፊት በሌሎች የተለያዩ የትምህርት ተቋማት ከተከሰተው ክስተት ጋር በሚመሳሰል መልኩ በትውልድ ትግራይ ነን የሚሉ ተማሪዎች በኦሮሞ ተማሪዎችና በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የንቀትና የጥላቻ ቃላት በኣደባባይ ኣሰሙ። ለዚህ የንቀትና የጥላቻ ጥቃት ምላሽ የሰጡ የኦሮሞ ተማሪዎች በስርኣቱ የኣጋዚ ልዩ ሃይል ተለይተው ተደበደቡ። በድብደባውም ለከፍተኛ የኣካል ጉዳት ተዳረጉ። እስከ ዛሬም ድረስ በዚህ ወቅቱ ድብደባ ሳቢያ ለኣካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት ተዳርገው የሚገኙ ተማሪዎች ኣሉ። ከዚያ ጠላታዊ ጥቃት ሸሽት ወደ ቤተሰቦቻቸው ለመመለስ ጊቢውን ለቀው የወጡ ተማሪዎችም ከየደረሱበት ተለቅመው ገሚሶቹ ታሰሩ ሌሎቹ ደግሞ ታፍነው ደብዛቸው ጠፋ። የዚህ ጥቃት ሰለባ የሆኑት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ይማሩ የነበሩ ሁሉም የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ነበሩ ማለት ይቻላል። ይህ ክስተት ወደ ሃረማያ፣ ኣርባ ምንጭና ወለጋ ዩኒቨርሲቲዎችም በመዛመቱ በርካታ የኦሮሞ ተማሪዎች ለጉዳት መዳረጋቸው ይታወሳል።

ጥር 5 ቀን 2013 በፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ

በቅርቡ በዚህ እለት በፍንፍኔ ዩኒቨርሲቲ አራት ኪሎ ጊቢ የተከሰተው ክስተትም ቀደም ሲል ከተጠቀሱት መሰል የትንኮሳና የጭካኔ እርምጃዎች የተለየ አይደለም። በወያኔ የደህንነት ሃይል በተቀናጀ መልኩ *"ጋላ ክፉ ህዝብ ነው"* የሚል ጽሁፍ በተማሪዎች ካፌቴሪያ፣ በኮሪደርና በተማሪዎች ማደሪያ (ዶርሚተሪ) ውስጥ ተጽፎ ተገኘ። የጥላቻ መልእክቱን የተመለከቱ የኦሮሞ ተማሪዎች ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ አመለከቱ። ይህን ለማጣራት ወደ ስፍራዎቹ የተላከው የፖሊስ ሃይል ወንጀለኞቹን ፈልጎ በቁጥጥር ስር በማዋል ፋንታ ጽሁፉን በተመሳሳይ ቀለም በመሰረዝ ማስረጃ በማጥፋት ተግባር ላይ አተኮረ። የኦሮሞ ተማሪዎች ይህንን ማስረጃ የማጥፋት ተግባርን አወገዙ። ዋነኛው አላማም የኦሮሞ ተማሪዎችን ነጥሎ መምታት በመሆኑ ሁከት በተቀሰቀሰበት ቅጽበት ተዘጋጅቶ ይጠብቅ የነበረው በአድልኦ የተሞላው የታጠቀ ሃይል ወደ ጊቢው ዘልቆ በመግባት የኦሮሞ ተማሪዎችን ለይቶ ያለ ርህራሄ እየደበደበ ወደ እስር ቤት አጋዘ። በዚሁ ድብደባ ሳቢያ አንድ የኦሮሞ ተማሪ መሞቱ ተረጋግጧል። ድብደባ የተፈጸመባቸው አብዛኞቹ ተማሪዎችም ጣረ ሞት ላይ ናቸው።

በጥቅሉ ሲታይ እነዚህ ጥቃቶች ከሶስት ዋና ዋና ነጥቦች የሚነሱ ናቸው። አንደኛው የወያኔ መንግስት በማንኛውም ሰአት የህዝብ ኣመጽ ሊቀሰቀስብኝ ይችላል በሚል ስጋት የተዋጠ በመሆኑ በተለይም በተማሪዎቹ ዘንድ ያለውን የኣብሮነት ስሜት ለመሸርሸር ሆን ብሎ የሚፈጽመው የከፋፍለህ ምታ ስልቱ ውጤት ነው። ሁለተኛውና ተያያዥ ነጥብ የሌሎች ብሄር ተወላጅ የሆኑ ተማሪዎች ኦሮሞን በጥርጣሬና በጥላቻ በመመልከት በነሱና በኦሮሞ መካከል የልዩነት ግንብ ተገንብቶ የተቃውሞው ሃይል ሚዛን ደካማና ሁሌም በቀላሉ በስርኣቱ ቁጥጥር ስር እንዲውል ለማድረግ የሚሸረብ ሴራ ነው። ሶስተኛው ኣላማ ደግሞ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚያነጣጥረው የጥላቻና የንቀት አመለካከት ካለፈው ስርኣት ተወርሶ እንዳለ እንዲቀጥል ለማስቻልና የኦሮሞ ልጆችም በተንበርካኪነት ስነ ልቦና ተሸብበው ጸጥ ብለው እንዲገዙ ለማስገደድ የሚደረግ ጥረት መሆኑ ነው።

ላለፉት 12 ኣመታት የወያኔ መንግስት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በተቀናጀ መልኩ በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ሲያቀነባብር የኖረው ሴራ ዋነኛ ኣላማው

1. የኦሮሞ ተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ እየረበሹ ተረጋግተው እንዳይማሩና ጥሩ የኣካዳሚ ውጤት እንዳያስመዘግቡ ማደናቀፍ
2. የኦሮሞን ህዝብ የነጻነት ትግል ኣላማ በማዛነፍ ትግሉ ፍትሃዊ መሰረት ያለው ሳይሆን በጭፍኑ በህዝቦች ጥላቻ ላይ ያተኮረ አስመስሎ ማቅረብ
3. የኦሮሞ ብሄርኝነትን መፈታተንና በመሰል ትንኮሳዎች የተማሪዎቹንና የህዝቡን ቅስም ለመስበር መሞከር
4. ሆን ብሎ ሁከት በመቀስቀስ በሰበቡ ጠንካራና ለብሄራቸው ክብር ተቆርቋሪ የሆኑ የኦሮሞ ተማሪዎችን አድኖ ለመምታት ያለመ ሆኖ ይታያል።

ይህ የወያኔ መንግስት የቀቢጸ ተስፋነት ጥረት ከቶ ሊሳካ አይችልም። የኦሮሞ ብሄርተኝነት በዚህ የፈሪዎች በትር አይኮላሽም። ኦሮሞን ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ጋር ለማጋጨት የሚደረገው ጥረትም አይሰምርም። ትልቁ መልእክታችን አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ከወያኔ ጋር ኣብረው ታሪካዊ ስህተት እየሰሩ የሚገኙት ሁሉ ከተያያዙት ከስህተት ጎዳና እንዲመለሱ ነው። የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ኣላማ በመንግስት ስርኣት ላይ ያነጣጠረ አንጂ በማናቸውም ብሄሮችና ብሄረሰቦች ላይ የጥላቻ ወይም የበቀል ስሜት ያዘለ ትግል ኣለመሆኑን ደግመን ደጋግመን ማስገንዘብ እንወዳለን። የኦሮሞ ህዝብ በሌሎች ዘንድ እንዲጠላ ለማድረግ ወያኔ የተያያዘው ጥረት መና የሚቀረው የትግላችንን ኣላማ ሳይገነዘቡ

በጭፍኑ በወያኔ ደጋፊነት የተሰለፉ ወገኖች ከድርጊታቸው ሲገቱ ይሆናል። ከዚህ ውጪ በኣሳፋሪ መልኩ ይህንን ጨቁዋኝ ስርኣት በመደገፍ በሚደረጉት ጸረ ነጻነት ኣንቅስቃሴዎች ሳቢያ ወደፊት በህዝቦች መካከል ሊከሰት ለሚችለው ኣሳሳቢ ኣደጋ የኦሮሞ ህዝብም ሆነ የነጻነት ትግሉ ተጠያቂ ሊሆኑ ኣይችሉም። ሊከሰቱ ለሚችሉት መሰል ኣደጋዎች ሃላፊነቱን መውሰድ ያለባቸው እንዲህ ያለውን ኣዳፋ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ በቀጣይነት የሚከተለው ስርኣትና በጭፍን ጥላቻ ተሞልተው ከስርኣቱ ጋር ኣብረው በኦሮሞ ህዝብና በነጻነት ትግሉ ላይ ጦራቸውን የሰበቁ ወገኖች ይሆናሉ። ማንኛውም ሰላማዊና ቅን ልቦና ያለው ወገን የሃገሪቷን ህዝቦች በሙሉ እየጨቆነና እየዘረፈ ባለው ኣምባገነን ስርኣት ላይ ኣነጣጥሮ መታገል እንዳለበት ማስገንዘብ እንወዳለን። የወቅቱ ኣንገብጋቢ ጥያቄም ይሄው ነውና!

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ

ጥር 9, 2013